# የቆሎ ት/ቤት - መካነ ቅኔ ሊቃውንት

ያሲን ዑመር

የኢትዮጵያ አዕምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት



## መግቢያ

ቅኔ፣ ሙዚቃ፣ ሥነ-ጽሑፍ ፣ ሥዕል ለሠለጠነም ሆነ በመሠልጠን ላይ ላለ አንድ አገር በእጅጉ አስፈላጊ ነው ፡፡ የቅኔውን መንገድ ብናውቀው ተወዳዳሪ የሌለው የቅኔ አዝመራ እናመርታለን፡ ፡ ከሙዚቃ ባህር እንደፈለግን መቅዳት ብንችል ስቃይን ልንታገስ የምንችልበትንና የትዕግስት ጣፋጭ ፍሬ የሆነችውን ታላቅ ደስታ የምንቀዳጅበትን መንፈስ እንፈጥራለን፡ ፡ የስነ-ጽሁፍ በረከትን መቋደስ ብንታደል በአንድ በኩል መጥፎ ልማድንና መጥፎ እምነትን፤ መጥፎ አስተዳደርንና መጥፎ ህግን በማስወገድ (በሌላ ወገን ከፍ ያለ ትምህርትና አብነት በመቅሰም) ተጭኖን የኖረውን ድንቁርና እናስወግዳለን፤መንፈሳችንን እናጎለምሳለን ( አቤ፤ 1962) ፡፡

በዚህ መነሻነት ለዕውቀት ያደላ፤ድንቁርናን የጠላ ብሩህና ብልህ ወላጅ ስለልጁ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ማሰብና ማስተዋል ያዘወትራል፡፡ የአብራክ ክፋይ ልጁ ዕውቀትና ጥበብን ፍለጋ እንዲተጋ ይመክራል፡፡ከቀደሙት አዋቂዎች የዕውቀትና የጥበብን ማዕድ በመቋደስ ስነጥበብን፤ስነጽሁፍንና ኪነጥበብን ገንዘቡ እንዲያደርግ ይዘክራል፡፡ በልጁ የአላዋቂነት ጨለማ ላይ የዕውቀት ብርሃን ወደሚፈነጥቅበትና የጥበብ ወጋገን ወደሚንተገተግበት የቆሎ ትምህርት ቤት ሄዶ እንዲማር ይፈቅድለታል፡፡ ልጁ በቆሎ ተማሪነት አንድ ያለውን የደበሎ ለባሽነት ጉዞ ደረጃ በደረጃ በንባብ ቤት፤ በቅዳሴ ቤት፤ በዜማ ቤት፤በቅኔ ቤትና በመጽሐፍ ቤት የዕውቀትና የጥበብ ጎዳና አቋርጦ የሊቃውንትነት ካባ ደርቦ “ይበል” እንዲሰኝለትና እንዲመረቅለት ይመኛል፡፡

ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ የማይናቅ አስተዋጽዖ ላደረገው ጥንታዊው የቆሎ ትምህርት ቤት ምስጋና ይግባውና እጅግ በርካታ ደበሎ ለባሽ ተማሪዎች የሊቃውንትነት ካባ ደርበው የየወላጆቻቸው ኩራት የሆኑባቸው ሁለት ሺህ ዘመናት ተቆጥረዋል፡፡ የማንነታችን መገለጫ የሆነው ይህ ጥንታዊ ት/ቤት አገሪቱ በተጓዘችባቸው ረጅም ዘመናት ተማሩ የተባሉትን ሊቃውንትና የሀገር መሪዎችን ያፈራ የተከማቸና የዳበረ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት ለትውልድ ያስተላለፈ የትምህርት ቅርስ የአበው ውርስ ነው(ዓለሙ፤1999)፡፡

እንደመታደል ሆኖ ሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በርካታ የቅኔ ሊቃውንት የተቀዱባት ባህር ናት፡፡ ሊቃውንቱ አዕምሮአቸው ቅኔ ምስጢር የሚያፈላ፤ ስነ-ልቡናቸው በዕውቀት የተመላ ነበሩ፡፡ ጥልቅና ምጡቅ በሆነ ተሰጥዖአቸው እየተመሩ የቅኔን አዝመራ ለፍሬ ያበቁም ነበሩ፡፡

ከላይ በጥቅሉ የቀረበውን መንደርደሪያ ታሳቢ በማድረግ በጥናታዊ ፅሁፉ በኢትዮጵያ ባህላዊ የትምህርት ስርአት ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸውን የቆሎ ተማሪ ምንነትና የቅኔ ትምህርት ሁለንተናዊ ገጽታ ለመዳሰስ ጥረት ይደረጋል፡፡በጥረቱም፤- የቆሎ ተማሪ ማነው ?ቅኔ ምንድን ነው ? የቅኔ አይነቶች ምን ምን ናቸው? የቅኔ ግዕዛዊ ዋና ዋና ክፍሎች ምንድን ናቸው? የቅኔዎቻችንን አዝመራ ለፍሬ ያበቁ ስመ-ጥር ባለቅኔዎች የት የት ይገኛሉ? እነማንስ ናቸው? ?የሚሉት ጥያቄዎች ይነሳሉ፡፡ በቅደም ተከተላቸው ምላሽ ያገኛሉ፡፡በመጨረሻም የሀገራችን የቆሎ ት/ቤትና የቅኔ ጥበብ መጻኢ ዕጣ ፈንታ ምን መሆን እንደሚገባው የሚጠቁም ማጠቃለያ ተካትቷል፡፡

## 1.1 የቆሎ ተማሪ ማነው ?

የቆሎ ተማሪ ማለት ለዕውቀት ሲል ከወገኑ ተለይቶ፤ቀዬውን ጥሎ፤ከሀገሩ ኮብልሎ፤ ከውሻ ጋር ታግሎ

ቢያገኝ ቁራሽ እንጀራ፤ቢያጣም ጥሬ ለምኖ፤ ደበሎ ለብሶ፤ አኩፋዳ ተሸክሞ፤ ጉዝጓዝ ተንተርሶ የሚኖር

ለቀለም የተሰደደ፤ ለጥበብ የሚንከራተት መፃኢውን ኩነት አርቆ ተመልካች ነው (ሊቀ-ጉባኤ ታረቀኝ በ“ብሌን” ቁ.4፤ 1999 ውስጥ) ፡፡

ከገለፃው የቆሎ ተማሪ ዕውቀትን ፍለጋ የባይተዋርነትን አደጋና የረሃብን አለንጋ የሚጋፈጥ መንፈሰ-ጽኑና ቆራጥ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ የሆዱን ረሃብ በመንፈሱ ጥጋብ የሚያካክስና ከጉስቁልናው አድማስ ማዶ በሚገኘው ሩቅ ነገ ውስጥ የዕውቀት ስንቁንና የጥበብ ትጥቁን አሻግሮ ማየት የሚችል ባለ ራዕይ መሆኑንም እንዲሁ፡፡

በሌላ በኩል የቆሎ ተማሪን ምንነት በውል ለመረዳት በአብዛኛው ከቤተሰቦቹ ጠፍቶ ከሚሄድበት አንስቶ ከመሰሎቹና ከመምህሩ ጋር እስካለው የአቀባበልና የአብሮ መኖር መስተጋብር ድረስ ያለውን ሂደት በጥልቀት መመርመር ተገቢ ነው የሚሉ ጥናትና ምርምር አድራጊዎች አሉ፡፡ ይህንን ሂደት ሊቀ-ጉባኤ ታረቀኝ (ጥቁም ሥራ)

እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡

> አንድ ተማሪ ወደ ማንኛውም የቅኔ ቤት ሲሄድ በአብዛኛው ከቤተሰቡ ተሰውሮ( ተደብቆ) ነው፡፡ የሚይዘው አንዲት አኩፋዳ፤ አንዲት ለምድና አንዲት ነጠላ አይሏት ጋቢ መለስተኛ ኩታ ሊሆን ይችላል፡፡ ስንቁ ግን የማርያም ስምና የገበሬው ችሮታ ነው፡፡…ተማሪው ከሄደበት ተማሪ ቤት ሲደርስ ተማሪዎች “ መኖር “ ብለው አክብረው ፤ እግሩን አጥበው ፤ ከለመኑበት አኩፋዳ ቁራሽ አዋጥተው መኝታ ለቀው ያሳድሩታል፡፡ በማግስቱ መምህሩ ፊት በተማሪዎች አለቃ አማካይነት ይቀርባል፡፡… መምህሩ ስሙንና የመጣበትን ምክንያት ጠይቀውና አረጋግጠው ጎጆና ባልደረቦች እንዲሰጡት ያዙለታል፡፡ የልመና መንደርም እንደሌሎቹ ወይም ከሌሎቹ ጋር ተካፍሎ ይከለልለታል፡፡ ትምህርቱንም ይቀጥላል፡፡ …. መጀመሪያ ግስ ያጠናል፤ ያጠናውን ግስና ነባር ቃላት በየዕለቱ ከሚዘረፈው ቅኔ ጋር በማነፃጸር ምስጢር ለማደላደል ይሞክራል፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ቅኔ ደረጃ ይደርሳል፡፡

በማለት ይዘረዝሩታል፡፡

የቆሎ ተማሪውን መከራና ችግር ቻይነትና ዕውቀትና ጥበብ ፈላጊነት ዕንባቆም(1958) እና ዓለሙ(1997) ይስማሙበታል፡፡ ይህንንም ተማሪው ከእናት አባት፤ ከዘመድ አዝማድ ከጓደኛና ወዳጅ ተለይቶ የተወለደበትንና ያደገበትን አካባቢ ትቶ ሩቅ አገር መሄድ ይኖርበታል፡፡ በጉዞው ዳገት መውጣት፤ቁልቁለት መውረድ፤እንቅፋት መመታት፤እሾህ መወጋት፤በቀን ሀሩር በሌት ቁር መንገላታት፤መራብና መጠማት ይኖራል፡፡ ቅኔ ቤት ከደረሰም በኋላ ቢሆን አብዛኛውን ጊዜ የዕለት ጉርሱን የዓመት ልብሱን የሚያገኘው “ በእንተ ስሟ ለማርያም፤ ስለቸሩ እግዚአብሒር ” ብሎ ለምኖ ከመንደር ውሻ ጋር ታግሎና ተከላክሎ፣ፈንጣጣ፣ ተስቦና ወባ በመሳሰሉትና በሌሎች የውሃ ወለድ በሽታዎች ተጠቅቶ ነው፡፡ ይህንንና የመሳሰለውን ችግር ለመቋቋም የሚችለው በዕድሜ የበሰለ ወጣት ሲሆን ነው፡፡…የቅኔ ትምህርት ደረጃው ከጸዋትወ ዜማ ቀጥሎ ከትርጓሜ መጻሕፍት አስቀድሞ በጉልምስና ወራት ነው፡፡ ምክንያቱም ትምህርቱ የረቀቀና የጠለቀ በመሆኑ የትውልድ ሀገሩን ትቶ ጎራ ዞሮ ወንዝ ተሻግሮ ወጥቶ ወርዶ ከውሻ ጋር ጦርነት ገጥሞ ቁራሽ እንጀራ ለምኖ ደበሎና ድሪቶ ለብሶ ብዙ ፈተና ተቀብሎ አይመስሉ መስሎ ቀይ የነበረው ጠቁሮ፤ ረጅም የነበረው አጥሮ ተጠምቶ ጸዋትወ መከራን ሁሉ ታግሶ የሚማሩት የተባህትወ ትምህርት ነው በማለት ያብራሩታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ጥናታዊ ጽሑፎች በጥቅሉ የሚጠቁሙት የቆሎ ተማሪው ዕውቀትና ጥበብን ፍለጋ ከረሃብ፤ ከጥማት፤ ከዕርዛትና ከባይተዋርነት ጋር በቆራጥ ወኔና በፅኑ መንፈስ የሚዋጋ የትምህርት አርበኛ መሆኑን ነው፡፡

## 1.2. የቅኔ ትምህርት ሁለንተናዊ ገጽታ

### 1.2.1. ቅኔ ምንድን ነው ?

ለቅኔ ምንነት ብያኔ ለመስጠት እጅግ በርካታ ጥረቶች የተደረጉ ሲሆን የሚከተሉት ለአስረጂነት ተጠቅሰዋል፡፡

ቅኔ ቀነየ ገዛ ካለው ግስ የተገኘ ወይም ቀነየ ገዛ ያለውን አንቀፅ ያስገኘ ጥሬ ዘር ነው( መልክአ ብርሃን አድማሱ፤ 1963 )፡፡

ቅኔ የሚባለው ጥሬ ዘር መነሻው መገኛው “ቀነየ ገዛ ካለው ግስ ሲሆን መገዛት ተብሎ በቀጥታ ይተረጎማል፡፡ ተቀነየ ለእግዚአብሄር በፍርሃት እንዲል፡፡ አገዛዙም እንዲሁ ሳይሆን በአዲስ ምሥጋና አመስግኑ ነው ‘‹ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ› ‹በማመስገን እንገዛለን› እንዲል መጽሐፉ (ጥዑመልሣን መኮንን፤ 1995፤19)፡፡

ቅኔ ማለት ግጥም አንድም የምስጋና ግጥም ማለት ነው( ሀብተማርያም፤1963፤172) ቅኔ የተለያዩና የተወሰኑ የዜማ ምጣኔዎች ያሉት እንደ ግጥም ቤት የሚመታ ይዘቱ ውበትና ጥልቅ ምሥጢር እንዲኖረው ተደርጎ በልዩ ልዩ የቅኔ መንገድ ዓይነቶች የሚቀናበርና በትምህርት አማካይነት የሚቀሰም ሥነ ቃላዊ ድርሰት ነው( አማርኛ መዝገበ ቃላት 1993፤180)፡፡

ቅኔ አንድ ቃል በሚሰጠው ቀጥተኛ ትርጉም ብቻ ሳይገታ ወይም ሳይወሰን አስመስለን ጥልቅ በሆነ የተደበቀ ምሥጢርን አጉልተን የምናይበት፤ የምንገልጽበት ዘዴ ወይም የአነጋገር ሥልት ነው (ዓለሙ 1997፤ 154) ፡፡

ቅኔ በሰምና በወርቅ በኅብርና በአንጻር በመነገር ሁለትና ሦስት ትርጉምን አዝሎ በኅብርና በምርምር ተጠማምሮ አንድን ምሥጢራዊ ሃሳብ ለመግለጽ የበቃ እንደሆነ ቅኔ ይባላል፡፡(ንጉሤ 1993፤1) ቅኔ በቁሙ ሙሾ፤ ግጥም፤ ቅንቀና፤ ቁዘማ፤ የፍትሐት የልቅሶ ዜማ፤ ማኅሌት፤ ጉማ ነው ( ኪዳነ ወልድ 1948፤798) ፡፡

ቅኔ የቅኔ ሊቃውንት በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊ ሐሳባቸውን የሚገልጹበት የምርምርና የፍልስፍና ድርሰት ነው ፡፡ ቅኔ በአጋጣሚ በተሰጥዖና በልማድ የሚደርሱት ድርሰት አይደለም ፡፡ የቅኔ ትምህርት ቤት ተከፍቶለት መምህር ተሰይሞለት ጉባኤ ተዘርግቶለት፤ ሥርዓተ ትምህርት ተዘጋጅቶለት ፤ ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ፤ ከመምህር መምህር ተመርጦ፤ደበሎ ለብሶ፤ ከውሻ ተከላክሎ፤ ቁራሽ ለምኖ፤ ቆሎ ቆርጥሞ፤ የመምህሩን ቅኔ አጥንቶና አስመስሎ ቆጥሮ ለመምህሩ አሳርሞ የሚማሩት ድርሰት ነው፡፡ ይህ በመሆኑ ቅኔ ትምህርታዊ ድርሰት ነው፡፡ ቢሆንም ግጥማዊነቱን አንርሳ ( ዜና ማርቆስ 1994፤2)፡፡

በመሆኑም ቅኔ ማለት ሲተረጎም ሰው ከራሱ አዕምሮ አንቅቶ ምስጋና ለማቅረብ ሲያስብና ምሳሌ መስሎ፤ ምሥጢር አሻሽሎ ፤ ግጥም በመግጠም የልቡናውን ዕውቀት ፤ የአዕምሮውን ርቀት የሚገልፅበት ፤ ዕውቀቱን የሚያስተምርበት ፤ የሰሚንም አዕምሮ የሚያነቃቃበትና የሚያስታውቅበት የግጥም ጥበብ ነው ፡፡ ቅኔ በቃልና በኅሊና የሚያዝ

እንጂ በወረቀት የማይሰፍር በውሣጤ አዕምሮ ከሚገኝ ከሂል ድንገት የሚገነፍል ልዩ ፀጋ ነው :: ቅኔ ኪነ ጥበብ ነው :: ቅኔ የኢትዮጵያዊነት አንድ አሻራ ነው :: ቅኔ የታሪካችን አካል ነው :: የቅኔው ሙያም በሌሎች ዓለማት የሌለ በሀገራችን ብቻ የሚገኝ የሀገራችን የጥበብ ቅርስ የአበው ውርስ ነው ::

## 1.2.2. የቅኔ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው ?

የቅኔ ዓይነቶችን ለማወቅ ሊቀ-ለቃውንት ያሬድ የሰጡትን ትንተና ማንሳት አስፈላጊ ነው:: ከትንተናቸው "የጎንጅ፤ የዋድላና የዋሸራ " ተብለው የሚታወቁ ሶስት የቅኔ አይነቶች መኖራቸውን ለመረዳት ይቻላል:: ሊቀ-ሊቃውንቱ ገለጻቸውን በመቀጠል የቅኔዎቹ ልዩነት በግስ አገሳሰስና እርባታ፤ በሚገቡና በማይገቡ የቃላት ጠባይ ፤ በዜማ ልክ፤ በቅኔ አገባብ ህግ፤ በቅኔ ስደራና በልውጥ ያሬዳውያን የዜማ ስፍሮች ወዘተርፈ መሆኑን ያብራራሉ:: አያይዘውም ለቅኔዎቹ አይነት መለያየት መነሻ የሆኑት "ጎንጅና ዋሸራ" የተባሉት ስፍራዎች በጎጃም፤ "ዋድላ" የተባለው መካነ ቅኔ ደግሞ በወሎ ክፍለ ሀገር መገኘታቸውን ይጠቁማሉ:: እነዚህ አውራጃዎች ለብዙ ዓመታት የቅኔ ትምህርት የአብነት ቦታ ሆነው በመቆታቸው ቅኔዎቹ በእነርሱ ስም ሊጠሩ መብቃታቸውን ይጠቅሳሉ::

በተጻራሪው ከነፈርግብ አታለል "የግዕዝ ቅኔያት ታሪካዊ አመጣጥና ዕድገት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ባቀረቡት መጣጥፍ የቅኔ ዓይነቶችንና ምሳሌዎችን ለመዳሰስ ጥረት አድርገዋል:: በጥረታቸውም የቅኔ መንገዶች ብዙ መሆናቸውን፤ በአጭር ጽሑፋቸው ሁሉንም መዘርዘር አስቸጋሪ መሆኑንና ከ300 በላይ መንገዶች እንደሚገኙ ገልጸ ማለፍ ግዴታ መሆኑን ያብራራሉ:: ከገለጸዎቹ መረዳት የሚቻለው የቅኔ ዓይነቶችን ወይም መንገዶችን ትክክለኛ ቁጥር ለማወቅ ጥልቅ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ነው::

## 1.2.3. የቅኔ ግዕዛዊ ዋና ዋና ክፍሎች ምንድን ናቸው?

ሊቀ-ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ማርቆስ / በአሁኑ ወቅት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ/ ግዕዛዊው ቅኔ ሰባት ዋና ዋና ክፍሎች እንዳሉት ይገልጻሉ:: የቅኔውም ስምና ሙያ፤ የቤቱ ልክና የሚባልበት ጊዜ፤የያንዳንዱም ቅኔ ትርጉምና አስተያየት ግዕዛዊው ቅኔ ሰባት ዋና ዋና ክፍሎች እንዲኖሩት የሚያደርጉ ዓበይት ምክንያቶች መሆናቸውን ያብራራሉ:: የቅኔ ዋና ዋና ክፍሎቹ:-

ጉባኤ ቃና------- ባለ ሁለት ቤት ነው:: እርሱም የትስብእትና የመለኮት ምሳሌ ነው፤ ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ለመሆኑ፤

ዘአምላኪየ-------- ሦስት ቤት ያለውና የሥላሴ ምሣሌያቸው፤

ሚበዝኀ----------- ሦስት ቤት ያለውና የሥላሴ ምሣሌያቸው፤

*ዋይ ዜማ---------- አምስት ቤት ያለውና የ5ቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሳሌ፤

*ሥላሴ ------------ ስድስት ቤት ያለውና የ6ቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ፤

*ዘይእዜ ----------- አምስት ቤት ያለውና የ5ቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሳሌ፤

*መወድስ --------- ረጅም ቅኔ ነው፤ ቤቱም ዘጠኝ ነው፤ የ9 ሐፁረ መስቀል ምሳሌ መሆናቸውን ይዘረዝራሉ::

*ሊቀ ጉባኤ ታረቀኝ ከላይ በተራ ቁጥር( 4-7) ስለቀረቡት የቅኔ ዋና ዋና ክፍሎች በመጠኑ የተለየ ትንታኔ ይሰጣሉ::

በትንታኔው መሠረት፤

4. *ዋይ ዜማ--------- ሦስትም አምስትም ቤት አለው፤

5. * ሥላሴ ሦስትም ስድስትም ቤት አለው፤

6. * ዘይእዜ--- ሦስትም ሰባትም ቤት አለው፤
7.*መወድስ -ኹለትም፤ሰባትም፤ስምንትም ቤት አለው ይላሉ::

## 1.2.4. የቅኔዎቻችንን አዝመራ ለፍሬ ያበቁ ስመ-ጥር ሊቃውንት የት የት ይገኛሉ? እነማንስ ናቸው?

በላይ (1996) "የቅኔ ከዋክብት " በሚለው የሥነ ግጥም መድብል ውስጥ የሀገራችን ስመ-ጥር የቅኔ ከዋክብት የት የት ይገኛሉ? የሚለውን ጥያቄ ያነሳሉ::

ያነሱትን ጥያቄም፤-

አዕምሮአቸው ቅኔ ምሥጢር የሚያፈላ፤
ሥነ-ልቡናቸው በዕውቀት የተሞላ፤
ነበሩ ሊቃውንት በላስታ በዋድላ፤
በአክሱም በጎንደር ፤ ግሸን ላሊበላ::
ረቂቁን ህዋስ የትርጓሜ ምሥጢር፤
አጉልተው ያሳዩ በቅኔ መነፅር፤
ነበሩ ከዋክብት በትግራይ በጎንደር፤
በወሎ በሸዋ ጎጃም በጌምድር፤
በመንዝና ግሼ በተጉለት አንኮበር፤
ምሥራቅ ኢትዮጵያ አርሲ ባሌ ሐረር፤
ሲዳሞ ወለጋ ከፋ ኢሊባቦር::
ሸዋ ተሻግሬም እስቲ ጥቂት ልጥቀስ፤
ከመንዝና ግሼ ሥላሴ በመለስ፤
እንደ ንጋት ፀሐይ እንደ አጥቢያ ኮከብ
ታሪካቸው ደምቆ ከሩቅ የሚነበብ፤
ነበሩ በሸዋ ከዋክብተ-ጥበብ::

በማለት ይመልሳሉ::

በዚህ አያበቁም፤ የሀገራችንን የቅኔ ከዋክብት መገኛ ሐሰሳቸውን፤-

ልቆጥራቸው ባልችል አንድ ባንድ ዘርዝሬ
የቅኔን አዝመራ ያበቁ ለፍሬ
ሊቃውንት ነበሩዋት ኢትዮጵያ ሀገሬ::

በማለት ቅኔ የመላይቱ ኢትዮጵያ ዘመን ዘለቅ የዕውቀትና ጥበብ ቅርስ የአበው ውርስ መሆኑን ያስገነዝባሉ::

በተጓዳኝ መገኛው በመላ ኢትዮጵያ የሆነውን የቅኔ አዝመራ ለፍሬ ያበቁ ሊቃውንት አንድ በአንድ በስም እያነሱ ያወድሳሉ:: የስመ-ጥር የቅኔ ሊቃውንት ውዳሴያቸውን:-

ጣና ዳር ቆሜ ዓባይ ወንዝ በመለስ፤
እስኪ ከመቃብር ሊቃውንት "ልቀስቅስ::

በማለት ይጀምራሉ::

በውዳሴያቸው የመጀመሪያ ምዕራፍ የጐጃምን የቅኔ ሊቃውንት ከትውልድ መንደራቸው ጋር በማቀናጀት ያሞጋግሳሉ:: ለአብነትም ተዋናይን ከጐንጅ ተራራ፤ መምህር ክፍለ ዮሐንስን ከአገው ምድር፤አራት ዓይና ጐሹን ከጐጃም፤ ገብረ ሥላሴን፡ ዮፍታሄ ንጉሴን፡ አባ ቴዎፍሎስንና

ዶ/ር ኢሳይያስን ከደብረ ኤልያስ፤ መልዓከ ፀሐይ ተገኜን ከአብማ፤ መምህር ውብሸትን ከብቸና፤ መልዓከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬን ከደብረ ዲማ፤ አለቃ ጌታሁንን ከሞጣ ጊዮርጊስ፤ መምህር ኢሳይያስና መምህር ሪሳታዎስን ከመርጦ ለማርያም፤ መምህር ቀስሙን ከደጋ ዳሞት፤ አለቃ ተክሌንና ማዕበሉ ፈንቴን ከዋሸራ ማርያም፤ መሪ ጌታ ጌቴን ከአዴት መድኃኔዓለም፤ አቤ ጉበኛን ከይስማላ ጊዮርጊስ፤ ዕቡይ ካሣንና ማዕበሉ ደሴን ከጐንጅ፤ሊቀ ኅሩያን ዘገዬን ከአዴት፤እማሆይ ገላነሽን ከጽላሎ አማኑኤል መቃብር በመቀስቀስ ማወደሳቸውን መግለጽ ይቻላል።

በቀጣዩ የውዳሴ ምዕራፍ ፈላስፋውን ዘርዓ ያዕቆብን ከአክሱም ፤ ደቀመዝሙሩን መምህር ወልደ ህይወትን ከእንፍራዝ ጎንደር፤በጽዮን ዘማሪ የቅኔ ፈጣሪ ፈላስፋ ተርጓሚና አስተማሪ የተባለለትን ዶሪን ከትግራይ ጨለቆት ሥላሴ፤ ዮሐንስ ገብላዊን ከወሎ አማራ ሳይንት፤ ሰባቱ ከዋክብት የተባሉትን እነ ድድቅ ወልዴን ከዋድላ ጨረቃ ዳውንት፤ የትርጓሜ ጠቢብ የቅኔ ነጐድጓድና የወሎ ነጸብራቅ የተባለለትን መምህር አካለወልድን ከቦሩ ሥላሴ፤ ለማን ከመቄት ደብረ አሮን መቃብር ቀስቅሰው ያወድሳሉ።

በሦስተኛው የውዳሴ ምዕራፍ አለቃ አባ ገብረ-ሐናን ከናበጋ ጊዮርጊስ፤ ጌቱ ገሞራውን ከጎንደር፤ አክሊሉን ከደምቢያ አዘዞ፤ራስ ወልደ ገብርኤልን ከትግራይ መኳንንት፤ ቀኛማች ተካልኝን ከወሎ መሳፍንት፤ ማዕበል ወልደ ሕይወትን ከጣና ዳር ሜጫ፤ ጥበቡ ገሜን ከደብረ ሊባኖስ ኩዩ መቃብር ቀስቅሰው ያወድሳሉ።

በአራተኛው የውዳሴ ምዕራፍ የትውልድ መንደራቸውን ያልጠቀሱላቸውን መንግስቱ ለማን፤ ዮሐንስ አድማሱን፤ ከበደ ሚካኤልን፤ ባለቅኔው ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅንን ከየመቃብራቸው ቀስቅሰው ያወድሳሉ። በመጨረሻም በላይ ሙታን የቅኔ ሊቃውንት የቀሰቀሱበትን የውዳሴ ምዕራፍ፤--

ልቆጥራቸው ባልችል አንድ ባንድ ዘርዝሬ

የቅኔን አዝመራ ያበቁ ለፍ ሊቃውንት ነበሩዋት ኢትዮጵያ ሀገሬ።

በማለት አጠናቅቀዋል።

በጥናታዊ ጽሑፉ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው በቆሎ ት/ቤት የቀሰመው የቅኔ ሙያ የዚህ ወይም የዚያኛው ብሔር ተብሎ የማይመደብና በሌሎች ዓለማት የሌለ የታሪካችን አንድ አካልና ማንነታችን መገለጫ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል።

## ማጠቃለያ

ሰው ዘርና የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ የረቂቅና ምጡቅ የቅኔ ጥበብ ሊቃውንት የሚማሩባት የቆሎ ት/ቤት (የመካነ ቅኔ ሊቃውንት) መገኛም ናት ። ለዘመናት የሊቃውንት ድሃ ሆና የማታውቀው እማማ ኢትዮጵያ በዘመነ ግሎባላይዜሽን የመካነ ቅኔ ሊቃውንት መገኛ የመሆኗን ብሥራት ነጋሪ የመፈለግ አዝማሚያ ማሳየት ጀምራለች።

በመሆኑም በቅኔ ጥበብ ዕውቀት የተካንንና በትምህርት ሥራ ዘርፍ የተሠማራን ባለሙያዎች ቅኔ የኢትዮጵያዊነት አንድ አሻራና የታሪካችን አካል መሆኑን ልናበሥርላት ይገባል። የቅኔው ሙያም በሌሎች ዓለማት የሌለ በሀገራችን ብቻ የሚገኝ የሀገራችን የጥበብ ቅርስ የአበው ውርስ መሆኑንም እንዲሁ። ከዚሁ ጋር በተጓዳኝ ጥንታዊው የቆሎ ት/ቤት የዘመናዊው ትምህርት ሥርዓታችን መደላድል እንደሆነም ለተተኪው ትውልድ መረጃውን የማቆየት አደራ እንዳለብን አምነን ለተግባራዊነቱ የየድርሻችንን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል።

በጥረቱም በዋናነት ሀገራዊው የቅኔ ሙያ ወጣቱ ትውልድ እንዲያውቀውና በተተኪው የነገ ትውልድ ውስጥም አብቦ እንዲያፈራ መደረግ ይኖርበታል። ለዚህም መምህራን ቅኔ በውጪውና በዓለማዊው ትምህርትና መጤ ባህል እየተበረዘ እንዳይሄድ ስለጥቅሙና ጥንታዊነቱ ማስተማርና ማስረዳት ይኖረባቸዋል። የጥናትና ምርምር ባለሙያዎች በዘመናዊ የመቅረጸ ድምጽና ምስል እየቀረጹና በጥልቀት እያጠኑ ለመጭው ትውልድ ለመዘክርነት ማስቀረት ይኖርባቸዋል። ሀገራዊው የቅኔ ሙያ በአዎንታዊ መልኩ አድጎ፣በልጽጎና ዳብሮ ለቱሪስት መስህብ እንዲሆንና ለኢኮኖሚው ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲወጣ መደረግ ይኖርበታል።

## የመረጃ ምንጮች መዘርዝር


ሀብተማርያም ወርቅነህ(1963)። ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት፤አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም፤ ማተሚያ ቤት።

ሊቀ ጉባኤ ታረቀኝ ደምሴ በ "ብሌን" ቁ.4፤ (1999)። "ግዕዛዊው የኢትያጵያ ቅኔ ከየት እስከ የት"

መልከአ ብርሃን አድማሱ(1963) "መጽሐፈ ቅኔ (ዝክረቃውንት)"፤አዲስ አበባ።

በላይ መኮንን (1996)። የቅኔ ከዋክብት፡ ሥነ-ግጥም፤ጣና ማተሚያ ቤት።

ዓለሙ ኃይሌ(1997)። "ጥንታዊ የቅኔ ትምህርት ቤት በኢትዮጵያ"።

አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993)። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፤አዲስ አበባ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

አቤ ጉበኛ(1966)። መስኮት፤አዲስ አበባ፤ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

ዕንባቆም ቃለ-ወልድ(1958)። "ስለቅኔ ትምህርትና ስለ ጥቅሙ "፤ለሦስተኛ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ ጥናት ጉባኤ የቀረበ፤አዲስ አበባ፤ያልታተመ።

ንጉሤ ነገዎ(1993)። "የቅኔ አፈታት ዘዴዎችና የምርምር ቅኔዎች ስብስብ "ሜጋ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።

ኪዳነ ማርያም ጌታሁን (1948) ። ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ፤አዲስ አበባ፤ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

ክነፈርግብ አታለል (1997) ። "የደበሎው ዓለም ት/ቤትና ተማሪዎች" በ "ፈለገ ጥበብ " መጽሔት

ዜና ማርቆስ እንዳለው(1994)። ቅኔ ለወጣቶች፤አዲስ አበባ፤ሆራይዘን ማተሚያ ቤት ።

ጥዑመ ልሣን መኮንን(1995) ።"ቅኔ፤ ፍኖተ ቤተ ክርስቲያን"፣ ጎንደር